DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

**የልጅ እድገት ሰራተኞች የትምህርት መስፈርቶች**
**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQs) ለቅድመ ልጅነት ሰራተኞች**

**ማርች 2023**

**የአጠቃላይ እይታ**

በዲሴምበር 2016፣ ሰራተኞች ትንንሽ ልጆችን ለማስተማር አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች እና የትምህርት ማስረጃዎች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE) ለቅድመ ልጅነት ሰራተኛ ሀይል የትምህርት መስፈርቶች የጨመሩ የተሻሻሉ የልጅ እንክብካቤ ፈቃድ አሰጣጥ ደንቦችን አሳትሟል። ለመሃል ዳይሬክተሮች፣ መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ የተስፋፉ የቤት ተንከባካቢዎች፣ የቤት ተንከባካቢዎች እና ተባባሪ የቤት ተንከባካቢዎች የትምህርት መስፈርቶች እና ስላሉት ግብዓቶች እና ድጋፎችን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከታች ይገኛል።

የOSSE የቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) እገዛ ዴስክ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት፣ ግብዓቶችን ለመጋራት፣ በእቅድ ላይ ለማገዝ እና ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የግለሰብ እርዳታ ለመስጠት ይገኛል። ለድጋፍ በ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም በ(202) 478-5903 የ OSSE ECE የእርዳታ ዴስክን ማነጋገር ይችላሉ።

**ዳራ እና የኋላ ታሪክ**

1. **OSSE ለዲሲ የቅድመ-ልጅነት የሰው-ኋይል ትምህርታዊ መስፈርቶችን ለምን ተግባራዊ እያደረገ ነው?**
   የመጀመሪያዎቹ ሶስት የህይወት አመታት ለልጅ አእምሮ በጣም ፈጣን እና ወሳኝ የእድገት ጊዜ ናቸው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የቅድመ ልጅነት ተሞክሮዎች ልጆች ለትምህርት ቤት እንዲዘጋጁ እና የዕድሜ ልክ፣ አወንታዊ ተፅእኖዎች እንደሚኖራቸው እና የአስተማሪ ብቃት በ በጥራት ላይ ተፅእኖ መኖሩን ነው። በ2016 የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦችን የማዘመን የOSSE ዓላማ በእንክብካቤ ውስጥ ያሉ ህፃናትን ጤና፣ደህንነት እና ጤንነት ለመጠበቅ እና የልጆችን ትምህርት የሚያዳብሩ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የመማሪያ አካባቢዎችን እና ልምዶችን ማዳበር ነበር። በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተካተቱት የትምህርት መስፈርቶች ሁሉም የቅድመ-ልጅነት አስተማሪዎች በልጆች እድገት ላይ ስልጠና እንዲኖራቸው እና በዋና መምህር ፣ የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ እና የዳይሬክተር ሚናዎች ላይ ያሉት ለህፃናት ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ልምዶችን ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ እውቀት እና ክህሎቶች እንዲኖራቸው በማረጋገጥ፣ እና ሌሎች ሰራተኞች ጥራት ያለው የቅድመ ትምህርት ፕሮግራሞችን እንዲሰጡ በመቆጣጠር እነዚህን ግቦች ይደግፋሉ።

2. **OSSE ለእያንዳንዱ የሰራተኛ ዓይነት የትምህርት መስፈርትን እንዴት ወሰነ?**
   በዲሴምበር 2016 የታተሙት የትምህርት መስፈርቶች በልጆቻችንን መንከባከብ ላይ ከተቀመጡት ሀገራዊ ምክሮች ጋር ይጣጣማሉ፥ ብሔራዊ የጤና እና የደህንነት አፈጻጸም ደረጃዎች፥ የቅድመ እንክብካቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች መመሪያዎች፣ በምርምር እና በሃኪሞች እና በባለሙያዎች እውቀት የተደገፈ። በዲሴምበር 2015፣ OSSE ለቅድመ ትምህርት ሰራተኞች የትምህርት መስፈርቶችን ለመጨመር የቀረበውን ደንብ-አወጣጥ በተመለከተ ግብረ መልስ ከቅድመ ትምህርት ማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላት ጠይቋል። OSSE ከዚህ በፊት የታቀደውን ደንብ እና ረቂቅ ግምገማዎችን ለማጣራት እና ለማሻሻል በባለድርሻ አካላት የተጋሩትን ግንዛቤዎች እና አስተያየቶች ተጠቅሟል።

**<u>የትምህርት መስፈርቶች</u>**

3. **ለእያንዳንዱ የሰራተኛ ዓይነት የትምህርት መስፈርት ምንድን ነው እና አስተማሪ መስፈርቱን መቼ ማሟላት አለበት?**
   ለእያንዳንዱ የሰራተኛ አይነት የትምህርት መስፈርት እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት ቀነ-ገደብ በሰንጠረዥ 1 ውስጥ ይገኛል።

**ሰንጠረዥ 1። መስፈርቶች ለልጅ እድገት ተቋማት ሰራተኞች**

| | የስራ መደብ | ዲግሪ/የምስክር ወረቀት | የተፈጻሚነት ቀን |
|---|---|---|---|
| ማዕከልን-መሰረት-ያደረገ | ዳይሬክተር | በቅድመ ልጅነት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ (የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፣ ወይም የቅድመ ልዩ ትምህርትን ጨምሮ) **ወይም** በቅድመ ልጅነት ትምህርት ቢያንስ 15 ሴሚስተር ክሬዲት ሰአታት ያለው በማንኛውም የትምህርት ዓይነት የመጀመሪያ ዲግሪ። | ዲሴምበር 2, 2022 |
| | መምህር | በቅድመ ልጅነት ትምህርት ተባባሪ ዲግሪ (ወይም የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች፣ ወይም በቅርብ ተዛማጅ መስክ) **ወይም** በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ 24 ሴሚስተር ክሬዲት ሰአታት በቅድመ ልጅነት የያዘ ተባባሪ ዲግሪ። | ዲሴምበር 2, 2023 |
| | ረዳት አስተማሪ | የልጅ እድገት ተባባሪ (Development Associate (CDA)) ወይም ተባባሪ ዲግሪ (ወይም ከዚ በላይ) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት ዘርፍ። | ዲሴምበር 2, 2023 |
| ቤትን- መሰረት-ያደረገ | የተስፋፋ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ | በቅድመ ልጅነት ትምህርት ተባባሪ ዲግሪ (ወይም የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ወይም በቅርብ ተዛማጅ የሆነ መስክ) **ወይም** ቢያንስ 24 ሴሚስተር ክሬዲት ሰአታት በቅድመ ልጅነት የያዘ በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ተባባሪ ዲግሪ። | ዲሴምበር 2, 2023 |
| | የቤት እንክብካቤ ሰጪ እና ተባባሪ የቤት እንክብካቤ ሰጪ | CDA | ዲሴምበር 2, 2023 |

4. **እኔ በዲሲ ውስጥ በOSSE ፈቃድ ባለው የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ እሰራለሁ፣ ነገር ግን እኔ ምን አይነት የሰራተኛ ዓይነት እንደሆንኩ እርግጠኛ አይደለሁም። ምን ማድረግ አለብኝ?**
   ስለእርስዎ የሰራተኛ አይነት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ ከአሰሪዎ ጋር ይነጋገሩ። የእርስዎ አሰሪ ይህንን መረጃ በቅድመ ትምህርት ፍቃድ መስጫ ክፍል (DELLT) ክፍል፣ የOSSE የልጅ እድገት ፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት የሆነው፣ ውስጥ መከታተል ይጠበቅበታል።

5. **እኔ ለሰራተኛ አይነቴ የትምህርት መስፈርቱን ለማሟላት በፕሮግራም ውስጥ የተመዘገብኩ የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ነኝ፣ ነገር ግን ፕሮግራሙን እስከ ዲሴምበር 2፣ 2023 አላጠናቅቀውም። ምን ማድረግ አለብኝ?**
   ለስራ መደብዎ የሚያስፈልገውን የትምህርት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚጠበቀው የጊዜ ገደብ እባክዎ ከአሰሪዎ ጋር ይነጋገሩ። የእርስዎ አሰሪ እርስዎን ወክሎ ለመታለፍ ማመልከት ይችላል። እባኮትን ያስተውሉ፣ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች በግል ለመታለፍ ማመልከት አይችሉም። መታለፎች በተቀጠሩበት የልጅ እድገት ተቋም መሪ መቅረብ አለባቸው።

6. **እኔ በልጅ እድገት ተቋም ውስጥ እሰራለሁ እና ለሰራተኛ አይነቴ የትምህርት መስፈርቱን አላሟላም። እኔ በአሁኑ ጊዜ የትምህርት መስፈርቱን ለማሟላት በፕሮግራም ውስጥ አልተመዘገብኩም። ምን ማድረግ አለብኝ?**
   ለሰራተኛ አይነትዎ የትምህርት መስፈርቱን ካላሟሉ እና የሚፈለገውን የትምህርት ምስክር ወረቀት ለማግኘት በአሁኑ ጊዜ የኮርስ ስራን እየተከታተሉ ካልሆኑ፣ እባክዎን የECE የእገዛ ዴስክ'ን በECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 በተቻለ ፍጥነት ያነጋግሩ። የECE እገዛ ዴስክ ለሰራተኛ አይነትዎ የትምህርት መስፈርት ለማሟላት እቅድ እንድያወጡ ሊረዳዎት ይችላል። እንዲሁም የECE እገዛ ዴስክ የሚፈለገውን የትምህርት ማስረጃ እንዲያገኙ እንደ ስኮላርሺፕ እድሎች ያሉ ሀብቶችን እና ድጋፎችን እንዲለዩ ይረዳዎታል።

7. **በመጨረሻው ቀነ-ገደብ ለሰራተኛ ዓይነቴ የትምህርት መስፈርቱን ካላሟላሁ ምን ይከሰታል?**
   ማንኛውም ፈቃድ ያለው የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ የፍቃድ እና የጤና እና የደህንነት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በOSSE የፈቃድ አሰጣጥ እና ተገዢነት ክፍል በሚደረጉ የክትትል ጉብኝቶች ላይ ይሳተፋሉ። አቅራቢዎች በየዓመቱ አንድ የታወቀ ጉብኝት እና አንድ ያልተጠበቀ ጉብኝት ይኖራቸዋል። የፈቃድ ሰጪው ስፔሻሊስት በጉብኝቱ ወቅት ችግሮችን ወይም ጥሰቶችን ካገኘ፣ ለሰራተኛ አይነታቸው የትምህርት መስፈርቱን የማያሟሉ ሰራተኞችን ጨምሮ፣ አቅራቢው የፍቃድ መስጫ እጥረት ይደርሰዋል። አቅራቢው የማስተካከያ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለውጦችን በሚፈለገው ቀነ ገደብ ማድረግ አለበት እና የሰራተኛው አባል ለስራ መደባቸው የሚፈለገውን የትምህርት መስፈርት ለማሟላት ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው (ለምሳሌ በCDA ፕሮግራም ውስጥ መመዝገብ ወይም በዲግሪ ፕሮግራም ውስጥ መመዝገብ ወዘተ.)። ስለ ልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ክትትል እና ቁጥጥር ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ እዚህ ይጫኑ።

8. **እኔ በልጅ እድገት ማዕከል መምህር ነኝ እና ከቅድመ ልጅነት ትምህርት ውጪ በሆነ ሌላ መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ አለኝ። ተባባሪ ዲግሪ ማግኘት አለብኝ?**
   በአሁኑ ጊዜ በቅድመ ልጅነት ትምህርት ያልሆነ ዲግሪ ካለዎት፣ በECE ውስጥ 24 የሴሚስተር ሰአታት እንዳጠናቀቁ ለማየት፣ ይህም ምንም እንኳን ዋና ትምህርትዎ በሌላ መስክ ቢሆንም የአስተማሪን አነስተኛ የትምህርት መስፈርት የሚያሟላ ሲሆን፣ OSSE የእርስዎን የትምህርት ማስረጃ(ዎች)ን መገምገም ይችላል። OSSE የትምህርት ማስረጃውን ይገመግማል፣ እና ብቁነቶቹ ከተሟሉ፣ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል። የግልባጭ ግምገማ ጥያቄ (ለምሳሌ፣ የትምህርት ምስክርነት ማረጋገጫ) በፕሮፌሽናል እድገት መረጃ ስርዓት (PDIS) በኩል በdcpdis.org፣ ተጠቃሚው አንዴ ከገባ በኋላ "ለትምህርት ምስክርነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አመልክት" የሚለውን ጠቅ በማድረግ ሊቀርብ ይችላል።

9. **ከቅድመ ልጅነት ትምህርት ውጪ በሆነ ሌላ መስክ ተባባሪ ዲግሪ አለኝ፣ CDA ማግኘት አለብኝ?**
   ከቅድመ ልጅነት ትምህርት ውጭ በሆነ ሌላ የትምህርት መስክ ተባባሪ ድግሪ ካለዎት፣ ለረዳት መምህር፣ የቤት ተንከባካቢ ወይም ተባባሪ የቤት ተንከባካቢ አነስተኛውን የትምህርት መስፈርት ያሟላሉ። ከእነዚህ የሰራተኞች አይነቶች ውስጥ ከሆኑ፣ የCDA ምስክር ወረቀት ማግኘት አያስፈልግዎትም። የማዕከል ዳይሬክተር፣ አስተማሪ ወይም የተስፋፋ የቤት ተንከባካቢ ከሆኑ፣ እባክዎን ጥያቄ 3ን ይመልከቱ።

10. **እኔ ከሌላ ሀገር ዲግሪ/የትምህርት ማስረጃ አለኝ። የትምህርት መስፈርቱን አሟላለሁ?**
   OSSE በውጭ ሀገራት የተሰጡ ዲግሪዎችን እውቅና ይሰጣል፣ የውጭ የትምህርት ማስረጃ ለUS እኩልነት እስከተገመገመ ድረስ። ይህ በ የብሔራዊ የምስክርነት ግምገማ አገልግሎቶች ማህበር (NACES) ወይም የአለም አቀፍ ምስክርነት ገምጋሚዎች ማህበር (AICE) ውስጥ ባሁን ጊዜ አባልነት ባለው ድርጅት በኩል መደረግ አለበት። የእነዚህ አይነት ድርጅቶች ምሳሌዎች የአለም የትምህርት አገልግሎቶች (ወርልድ ኢዱኬሽን ሰርቪስስ (WES)) እና SpanTran ናቸው። ስለ የውጭ አገር የትምህርት ምስክርነት ግምገማዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የመረጡትን የNACES ወይም AICE ድርጅት ማነጋገር ይችላሉ። ግምገማውን/ትርጉሙን ለማካሄድ ለመረጡት ሻጭ መክፈል ያለብዎት የውጭ ሀገር የትምህርት ምስክርነት ግምገማ እና/ወይም ትርጉም ጋር የተያያዘ ክፍያ ሊኖር ይችላል። ተመዛዛኝነትን ለመገምገም ድርጅትን መለየት ላይ ድጋፍ ለማግኘት የECE የእገዛ ዴስክ በECE help desk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ማግኘት ይችላሉ።

እባክዎን ያስተውሉ፣ የ[ዲሲ መሪ አስተማሪዎች ለከፍተኛ ዲግሪዎች (ዲሲ ሊድንግ ኢዱኬተርስ ቱዋርድ አድቫንሲድ ዲግሪስ (DC LEAD)) ፕሮግራም] የውጪ የትምህርት ማስረጃ ግምገማ እና/ወይም ለትርጉም ወጪን ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፣ ለኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ወይም ዲግሪ ለማጠናቀቅ የሚጠቀሙበት ከሆነ ወይም አነስተኛውን የትምህርት መስፈርት ለማሟላት ክሬዲቶች ካስፈለጉዎ። ስለ DC LEAD የውጭ የትምህርት ምስክርነት ትርጉም እና ምዘና ድጋፎች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን DCLEAD በDCLAAD@sechildrensfund.org ወይም (202) 561-5500 ያግኙ።

11. **እኔ ለረጅም ጊዜ የቅድመ ልጅነት ትምህርት ላይ ሰርቻለሁ። በልምድ ላይ ተመርኩዞ ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች መታለፎች አሉ?**
ከዲሴምበር 2006 ጀምሮ ወይም ከዚያ በፊት በተመሳሳይ (ወይም በተነፃፃሪ) ሚና/የስራ መደብ ላይ ያለማቋረጥ፣ ያለ ትልቅ የአገልግሎት ክፍተት፣ ያገለገሉ የመሃል ዳይሬክተሮች፣ የተስፋፉ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎች እና አስተማሪዎች ለ[የ10-አመት ተከታታይ አገልግሎት መታለፍ] ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የ 10 ዓመታት ተከታታይ አገልግሎት መታለፍን ለመቀበል፣ የማእከል ዳይሬክተር፣ የተስፋፋ የቤት ተንከባካቢ ወይም አስተማሪ የ10 ዓመታት ተከታታይ አገልግሎት እንደነበራቸው የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች ታትመው ከወጡበት ዲሴምበር 2016 ጀምረው ማሳየት አለባቸው። ይህ ልምድ ግዴታ የቅድመ ልጅነት አስተማሪው ባሁን ጊዜ በተቀጠረበት እራሱ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ መሆን አያስፈልገውም። ሁሉም መታለፎች በተቋሙ መሪ መቅረብ አለባቸው። መታለፎች በጉዳይ-በ-ጉዳይ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ እና ዋስትና አይሰጣቸውም። OSSE በመተዳደሪያ ደንቦቹ መሰረት ምህረትን የመስጠት ወይም የመከልከል መብቱ የተጠበቀ ነው። ሁሉም የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ያሉትን የትምህርት እድሎች እንዲጠቀሙ በጥብቅ ይበረታታሉ።

## አዲሱን የትምህርት መስፈርቶች ለማሟላት ያሉ ድጋፎች

12. **እኔ ለሰራተኛ አይነቴ የትምህርት መስፈርቱን ለማሟላት CDA ማግኘት አለብኝ። የCDA ምስክርነት ለማግኘት ምን ድጋፎች አሉ?**
ያለ ምንም ክፍያ የ CDA የትምህርት ምስክርነት ለማግኘት ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ብዙ አማራጮች አሉ። OSSE ሁለት ፕሮግራሞችን ይደግፋል፣ የመጀመሪያ፣ እድሳት ወይም የቡድን ላልሆነ የCDA ምስክርነት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች የነጻ፣ በአካል እና/ወይም ድብልቅ የCDA ስልጠና እና የቅድሚያ ፕሮግራሞችን በሚያቅርቡ በ [CentroNía እና ሳዝኢስት ቺልድሬንስ ፈንድ] የሚሰራ። CentroNia በእንግሊዝኛ፣ በስፓንኛ እና በአማርኛ የCDA ስልጠና እና ዝግጅት ይሰጣል። ለበለጠ መረጃ፣ የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ CDA አስተባባሪ የሆኑትን ጄኒፈር ሳልጋዶ በjsalgado@centronia.org ወይም (202) 948-6851 ወይም ካሚላ ጆንሰን፣ የፕሮግራም አስተዳዳሪን በsoutheastcda@gmail.com ወይም (202) 561-1100 ያነጋግሩ። ሌላው አማራጭ በ[Quorum eLearning]፣ የCDA የትምህርት ምስክርነት ለማግኘት ወይም ለማደስ የሚያስፈልጉትን 120 የሥልጠና ሰዓቶችን ያካተተ በአባልነት ላይ የተመሰረተ የመስመር ላይ ሙያዊ እድገት መድረክ፣ በኩል ይቀርባል። Quorumን በመጠቀም የCDA የትምህርት ምስክርነት እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ላይ [መመሪያ መፅሃፍ] ይገኛል። Quorum በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በHelp@QuorumLearning.com ወይም (404) 325-2225 ያነጋግሩ። እባክዎን ያስተውሉ፣ በOSSE በሚደገፈው ፕሮግራም CDA የሚከታተል ሰው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ሊኖረው እና የዲሲ ነዋሪ መሆን ወይም በዲሲ ውስጥ በልጅ እድገት ተቋም ውስጥ መሥራት አለበት።

እንዲሁም፣ እንደ [Briya Public Charter School]፣ [United Planning Organisation](UPO)፣ [University of the District of Columbia's (UDC) የሥራ ኃይል ልማት ክፍል እና የዕድሜ ልክ ትምህርት]፣ [Trinity Washington University] እና [American University] ያሉ በዲሲ አካባቢ የCDA የትምህርት ምስክርነት/ማስረጃ የኮርስ-ስራ የሚሰጡ ሌሎች በርካታ አማራጮች አሉ። ከእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ አንዱን ለመከታተል ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ፕሮግራሙን በቀጥታ ማግኘት አለባቸው።

ለእርስዎ ትክክል የሆነውን የCDA ፕሮግራም ለመወሰን ድጋፍ ለማግኘት፣ የ [ECE የእገዛ ዴስክ] በECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።

13. **የ CDA የትምህርት ምስክርነት ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**
አንድ ሰው CDA ለማግኘት የሚፈጀው ጊዜ በግለሰቡ እና በተመረጠው ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ ነው። በተለምዶ፣ CDA ለማግኘት ሁሉንም መስፈርቶች ለማሟላት ከስድስት ወር እስከ አንድ አመት ሊፈጅ ይችላል።

14. **የCDA የትምህርት ምስክርነት በመስመር ላይ ለማግኘት አማራጮች አሉ?**
አዎ። Quorum eLearning የCDA የትምህርት ምስክርነት ለማግኘት ወይም ለማደስ የሚያስፈልጉትን ሁሉም 120 የሥልጠና ሰዓቶችን ያካተተ በአባልነት ላይ የተመሰረተ የመስመር ላይ ሙያዊ እድገት መድረክ ነው። አንዴ ብቁ የሆነ የቅድመ ልጅነት አስተማሪ የCDA ኮርስ ስራን እንደጨረሰ፣ የOSSE CDA ቾሮታዎች፣ CentroNia እና ሳውዝኢስት ቺልድሬንስ ፈንድ (የደቡብ-ምስራቅ የልጆች ፈንድ)፣ የCDA ፖርትፎሊዮ እና ግምገማን ለማጠናቀቅ የገንዘብ ድጋፍ እና እርዳታ ሊሰጡ ይችላሉ። Quorum (ኮረም)ን በመጠቀም የCDA ምስክርነት ማግኘት እንዴት እንደሚቻል ላይ ተጨማሪ መረጃን በዚህ መመሪያ መጻህፍት ውስጥ ማግኘት ይቻላል። ስለ Quorum ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ Help@QuorumLearning.com ወይም (404) 325-2225 ያነጋግሩ። እባክዎን ያስተውሉ፣ አንድ በQuorum አማካኝነት CDA የሚከታተል ሰው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማጠናቀቂያ ዲፕሎማ ሊኖረው እና የዲሲ ነዋሪ መሆን ወይም በዲሲ ውስጥ በልጅ እድገት ተቋም ውስጥ መሥራት አለበት።

15. **የተባባሪ ወይም የባችለር ዲግሪ መስፈርትን ኮረምን በመጠቀም ማጠናቀቅ ይቻላል?**
አይ። የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የCDA የትምህርት ምስክርነት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን 120 ሰዓቶች ለማጠናቀቅ ኮረም መጠቀም ይችላሉ። የCDA ኮርስ ስራን በQuorum አማካኝነት የሚያጠናቅቁ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች፣ CDA ለማግኘት ከሌሎች መስፈርቶች በተጨማሪ፣ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተመዘገቡ ፣ የCDA የኮርስ ሥራ (ለተጨማሪ መረጃ ጥያቄ 16 ይመልከቱ) በማጠናቀቃቸው መሰረት ለተባባሪ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ የሚያገለግሉ የኮሌጅ ክሬዲቶችን ሊያገኙ ይችላሉ።

16. **እኔ የCDA የትምህርት ማስረጃ አለኝ። በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ ክሬዲቶች ላይ እንደተጨማሪ ሊቆጠር ይችላል?** በዲሲ ክልል ውስጥ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች (ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ሜሪላንድ፣ ቨርጂኒያ) CDAን ለኮሌጅ ክሬዲት ለመቀበል የተለያዩ መስፈርቶች አሏቸው። የተመዘገቡበትን ዩኒቨርሲቲ ወይም ለመመዝገብ ፍላጎት ያለዎት ዩኒቨርሲቲን በቀጥታ ማነጋገር እና የCDA የትምህርት ምስክር ወረቀት ላለው ሰው ምን ያህል የኮሌጅ ክሬዲት ሊሰጥ እንደሚችል እና ሌሎች ማንኛውም ተያያዥ ወጪዎችን ወይም መስፈርቶችን መጠየቅ የተሻለ ነው።

17. **ተባባሪ ወይም ባችለር ዲግሪ በሚፈልጉ እንደ ማእከል ዳይሬክተሮች፣ የማእከል አስተማሪዎች እና የተስፋፋ የቤት እንክብካቤ ሰጪዎች ያሉ የሰራተኛ ዓይነቶች ውስጥ ተቀጥሮ ለሚሰራ የልጅ እድገት አስተማሪ ለኮርስ ስራ ለመክፈል የስኮላርሺፕ እድሎች አሉ?**
OSSE ትምህርት መቀጠል ውድ ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባል እናም የሚፈለጉትን የትምህርት ማስረጃዎች ለማሳካት የዲሲ የቅድመ የልጅነት ጊዜ ሰራተኞችን ለመደገፍ የወሰነ ገንዘብ፣ ጊዜ እና ግብአቶች አሉት። ተባባሪ ወይም ባችለር ዲግሪ ለሚከታተሉ ግለሰቦች የስኮላርሺፕ ዕድሎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥
- የDC Futures ፕሮግራም ለሁሉም ተሳታፊዎች ለማጠናቀቅ የግል እና የገንዘብ እንቅፋቶችን የሚፈቱ ከኮሌጅ ማሰልጠኛ እና የድጋፍ አገልግሎቶች በተጨማሪ የመጨረሻ ዶላር ስኮላርሺፕ (የትምህርት ክፍያ፣ ሌላ ክፍያ እና ወጪ) በሦስት የሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች በመስጠት የዲሲ ኮሌጅ ተማሪዎች የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲያጠናቅቁ ይረዳል።
- የMayor's Scholars የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የመጀመሪያ ተባባሪ ወይም ባችለር ዲግሪያቸውን በተመረጡ የአካባቢ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ለሚያገኙ ብቁ የዲሲ ነዋሪዎች በአስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። ፕሮግራሙ የመጨረሻ-ዶላር ሽልማት ሲሆን ይህም በተማሪው የገንዘብ ድጋፍ ጥቅል እና የመከታተል ወጪ መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት ሊያገለግል ይችላል።
- DC Tuition Assistance Grant (DCTAG) የተማሪ-ደረጃ የድጋፍ ፕሮግራም ሲሆን ብቁ ለሆኑ የዲሲ ነዋሪዎች በህዝብ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ከስቴት-ውስጥ እና ከስቴት-ውጪ

የትምህርት ክፍያ መካከል ያለውን ልዩነት እስከ $10,000 የሚደርስ የገንዘብ ድጎማዎችን ይሰጣል።
    - ለ Mayor's Scholars የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ወይም ለ DC Futures ፕሮግራም ለማመልከት ካቀዱ፣ OSSE መጀመሪያ ለ DCTAG እንዲያመለክቱ ይመክራል።
- የDC LEAD ፕሮግራም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ የልጅ እንክብካቤ አስተማሪዎች በቅድመ ልጅነት ትምህርት ተባባሪ እና/ወይም ባችለር ዲግሪ ለማግኘት የኮርስ ስራ እንዲያጠናቅቁ ነጻ የትምህርት እድል እና ማበረታቻ ይሰጣል።

እነዚህ የትምህርት እድሎች እና ሌሎች ግብዓቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ በ osse.dc.gov/eceresourcesሊገኝ ይችላል። ለእርስዎ ትክክል የሆኑ የስኮላርሺፕ እድሎችን መለየት ላይ ድጋፍ ለማግኘት፣ እባክዎን የ ECE የእገዛ ዴስክን በ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ

**18. ተባባሪ ወይም የባችለር ዲግሪ ለማግኘት የመስመር ላይ የዲግሪ አማራጮች አሉ?**

በመስመር ላይ የሚቀርቡ በርካታ የተባባሪ እና ባችለር ዲግሪ ፕሮግራሞች አሉ። በዲሲ አካባቢ ያሉ የኦንላይን ፕሮግራሞች ሊኖራቸው የሚችለው የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች በሚከተሉት ድረ-ገጾች ላይ የፕሮግራም ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፥

- የማዕከል ዳይሬክተር፥ osse.dc.gov/page/center-director
- አስተማሪ፥ osse.dc.gov/page/teacher
- የተስፋፋ የቤት እንክብካቤ ሰጪ፥ osse.dc.gov/page/expanded-home-caregiver

ስለነዚህ ፕሮግራሞች ጥያቄዎች ያላቸው የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ፕሮግራሙን በቀጥታ ማነጋገር አለባቸው።

## <u>ክፍያዎች/ደመወዝ</u>

**19. የትምህርት ማስረጃዬን ካሳካሁ በኋላ፣ ከAidKit ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድ ተጨማሪ ገንዘብ አገኛለሁ?**

በ2023 የበጀት ዓመት (FY23)፣ ከኦክቶበር 1, 2022 እና ሴፕቴምበር 30, 2023 የሚደረገው፣ OSSE እና AidKit በ የቅድመ ልጅነት አስተማሪ የክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ በኩል ብቁ ለሆኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ተጨማሪ ክፍያዎችን በቀጥታ እያሰራጩ ነው። በ FY23፣ ብቁ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እስከ አራት ክፍያዎችን መቀበል ይችላሉ። የቅድመ ልጅነት መምህር የሚቀበለው የክፍያ መጠን በሠራተኛ ዓይነታቸው እና የቅጥር ሁኔታ (ለምሳሌ የትርፍ ሰዓት እና የሙሉ ጊዜ) ላይ የተመሠረተ ነው። የአንድ አስተማሪ የሰራተኛ አይነት መሰረት ያደረገው በተቀጠሩበት ተቋም ሃላፊነቶቻቸው እና በብቁነታቸው ነው። የሰራተኛ አይነትዎ ከሜይ 15፣ 2023 በፊት (ሩብ ሶስት የመጨረሻ ቀነ-ገደብ) ወይም ኦገስት 15 (ሩብ አራት ቀነ-ገደብ) ከተቀየረ እና በአሰሪዎ በDELLT ውስጥ ከተሻሻለ፣ ለዚያ የሰራተኛ አይነት የክፍያ መጠን ይደርስዎታል። *እባክዎን አንድ ዲግሪ ወይም የምስክር ወረቀት ማጠናቀቅ ወዲያውኑ ወደ አዲስ የሰራተኛ አይነት እንደማይወስድዎት ያስተውሉ፥ ይህ* በተቋሙ ውስጥ ባለዎት ኃላፊነት እና የአሰሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ አሰሪዎ የሚሰጠው ውሳኔ ነው።

ከኦክቶበር 1፣ 2023 ከሚጀምረው 24ኛው የበጀት አመት ጀምሮ፣ OSSE ለልጅ እድገት ተቋማት ገንዘብ ወደ ማከፋፈል ይሸጋገራል፤ ገንዘቦችን የሚቀበሉ ተቋማት የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ተመጣጣኝ የካሳ ግብረ ኃይል ምክሮችን የሚያንፀባርቅ ደመወዝን ብቁ ለሆኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸዋል፣ ይህም በሠራተኞች ዓይነት እና ምስክርነቶች ላይ በመመስረት ለሠራተኞች ከፍተኛ የካሳ ክፍያን የሚያካትት ይሆናል። ስለእነዚህ ደሞዞች እና ለአቅራቢዎች እና ብቁ ለሆኑ ሰራተኞች መስፈርቶች ተጨማሪ መረጃ በፀደይ 2023 ይገኛል።

**20. አሰሪዬ ምን እንዲከፍለኝ ይጠበቅበታል?**

ማንኛውም ፈቃድ ያለው የልጅ እድገት ተቋም ሁሉንም የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የዲሲ መንግስት ህጎችን እና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለበት። ይህ በዲሲ የተቀመጡትን ዝቅተኛውን የደመወዝ ክፍያ እና የኑሮ ደረጃ ደሞዝ ተመን ይጨምራል። ስለ ዝቅተኛው የደመወዝ እና የኑሮ ደረጃ ደመወዝ ተመን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣እባክዎ የደሞዝ ሰዓት ተገዢነትን ድህረ ገጽን ይጎብኙ።

ከFY24 ጀምሮ (ከኦክቶበር 1፣ 2023 - ሴፕቴምበር 30፣ 2024 የሚሰራው) በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድ ውስጥ የሚሳተፉ የልጅ እድገት ተቋማት የሰራተኞቻቸውን ደመወዝ ወይም በፈንዱ የሚፈለገውን ዝቅተኛ ተመን የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞችን እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። ስለ ፈንዱ ተጨማሪ መረጃ፣ ሰራተኞች በደመወዛቸው ከፍ ያለ ማካካሻ ለማየት የሚጠብቁበትን የጊዜ ሰሌዳ ጨምሮ፣ በፀደይ እና በበጋ 2023 ይገኛል። አሰሪዎች በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት ፈንድ ውስጥ እንዲሳተፉ አይገደዱም፣ እና የልጅ እንክብካቤ አሰሪዎች በፈንዱ ውስጥ እንዲሳተፉ የምዝገባ ሂደት ገና አልተጀመረም። ቀጣሪዎ በፕሮግራሙ ውስጥ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ በ2023 በጋ ወይም በልግ ማየት ያስፈልግዎታል።